# በሰለጠነው ዓለም የማይሰለጥኑት ግለሰቦች ምን ይሻላቸዋል?

## ከኢትዮ-ኦብዞርቨር ስታፍ ሪፖርተር

## ሲያትል ዋሽንግተን

አንድ ማሕበረሰብ ወይም ግለሰብ ሰልጥኗል የሚባለው ምንና ምን ሲያሟላ ይሆን? ይህ ጥያቄ ጥልቅና ሰፊ ትንታኔ የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ለአንባቢዎች ግንዛቤ የሚስጨብጥ አጠር ባለ መልኩ ለመግለፅ እሞክራለሁ። ሰው ከሰው ይማራል እንደሚባለው ሁሉ፡ ማንኛውም ሰው እውቀት የሚቀስመው ከሰውና ከማሕበረሰብ መሆኑ የሚካድ ባይሆንም፣ ሰላምና ዲሞክራሲ በሰፈነበት አገር፣ በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ ድምፅ ማሰማት እየተቻለ፣ ባንዴራ አንግቦ፣ የሰው መብት መግፈፍና መዝለፍ፣ ከኢትዮጵያዊነት ጨዋነትና አንደበት ውጭ አስፀያፊ ስድብ መሳደብ፣ በወገን ላይ ምራቅ መትፋትና፣ ተሰባስቦ ወገን ለመደብደብ መሰለፍ የወንጀለኞች ተግባር እንጂ ሰላማዊ ሰልፍ ሊሆን እንደማይችል ለማንም ግልፅ ይሁን። ለመሆኑ ስብሰባውን በመሳተፍ ጥልቅና ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ መጠየቅና ድምፅ ማሰማት እየተቻለ፣ በራፍ ላይ መጮህ ዜግነታዊ መብት ይሁን እንጂ፣ አስፈላጊነቱ ግን አይታየኝም። ከምንኖርበት ማሕበረሰብ የምንማር ከሆነ፣ አንድ ቡድን ወይም ግለሰብ፣ ስብሰባውን መካፈል እስካልተከለከለ ድረስ ሰላማዊ ሰልፍ የሚወጣበት ምክንያት ይኖረዋል ብዬ አልገምትም። ያም ሆኖ፣ ውጭ መሰለፉና መጮሁ እንደሱስ ተቆጥሮ ቢተገበርም፣ በወገን ላይ ምራቅ ሳይተፉ፣ አስፀያፊ ስድብ ሳይሳደቡ፣ ወገን ለመደብደብ ሳይሞክሩ፣ በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ መተግበሩ ለተተኪው ትውልድ ትምህርት ይሰጣል ብቻ ሳይሆን ለባዕድም የኢትዮጵያውነት ጨዋነት ማንፀባረቅ ጥሩ አጋጣሚ ነበር እላለሁ። ይሁንና ማንኛውም ዓይነት ተግባር ሲፈፀም የተግባሩ መገለጫ ፈፃሚው ነውና፣ በህፃናት ፊት የተከሰተውን ሁሉ መከሰት፣ ልጆቻችን ምን ይማሩበታል ብሎ ማሰብ የሰለጠነና ትርጉም ያለው አስተሳሰብ ነበር። ታድያ ለልጆቻችን የምናቀስመው ትምህርትና እውቀት፣ በወገን ላይ ምራቅ መትፋትና መደባደብ ነው? ሙሉ ወይንም ግማሽ ዕድሜያችን ምዕራብ አገር የኖርነው ይህንን ለመማር ነው? በእጅጉ ያሳዝናል። ይልቁንስ የሰው ልጅ አላፊ (Perishable) ነውና መቼውንም ቢሆን ለልጆቼ ምን ትቼ አልፋለሁ ብሎ መገምገም አርቆ አሳቢነትና

አስተዋይነት እንጂ ሞኝነት አይደለም። ያም ሆኖ ሓሙስ ነሓሴ 24፣ 2006 በነ አቶ አዲሱ ለገሰ የኢትዮጵያ ምክትል ጠ/ሚ/ርና የገጠር ልማት ሚ/ር በስያትል የተካሄደው ስብሰባ ያሉንን ጥያቄዎችና ስጋቶች ተንትነን መልስ የምናገኝበት ጥሩ አጋጣሚ ከመሆኑም ባሻገር የወገኖቻችን አጠቃላይ ሁኔታም በቅርቡ የምንገነዘብበት መልካም ዕድል ነበር የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ከባህላችን የወረስነው ባይሆንም አብዛኞቻችን የመናገር እንጂ የመስማት ባህርይ ይጎድልብናል። ስለሆነም ባንድ ላይ ማጩብጨብ እንጂ ባንድ ላይ መናገር ፍሬ ቢስ መሆኑ ተገንዝበን፣ ያለምናቸው ዓላማዎችም ስኬት እንዲኖራቸው ምቹ ሁኔታ የምንፈጥርበት አጋጣሚ በዚሁ ስብሰባ ነበር። ስብሰባው ከተካፈሉት ወገኖች መረዳት እንደተቻለው፣ በወንጀል ተግባር ላይ የተሳተፉ አንዳንዶቹ፣ ውጭ ሆነው ወንጀል ለመፈፀም፡ እውስጥ ገብተውም ደግሞ ለመሳደብ ዕድሉ ስለተሰጣቸው፣ ከልክ ያለፈ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ስብሰባ እንደነበር ከአስተያየት ሰጪዎች መረዳት ችለናል። ይሁንና በሰለጠነው ዓለም ጠቃሚና ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ጠይቆ ውይይቱ አዝናኛና ትምህርት ሰጪ ማድረግ ሲቻል፣ የአመፀኞች ዲስኩር የሚሰማበት አጋጣሚ እንደነበር ተሳታፊዎቹን አስቆጥቷል የሚሉ ወገኖች አሉ። ኢትዮጵያዊነት ማለት በሰለጠነው ሃገር ባንዴራ አንግቦ በስሜት ተገፋፍቶ በማያስፈልግ ንትርክና የወንጀል ተግባር ተሳታፊ በመሆን ራስን አደጋ ላይ መጣል ነው እንዴ? ኢትዮጵያውነት ማለት በወገን ፊት ላይ ምራቅ መትፋት እንዲሁም ወገን ለመደብደብ መሞከር ነው? ያም ሆነ ይህ ግን በወንጀል ተግባር ላይ የተሳተፉት ግለሰቦች ተገቢ ቅጣት ያገኛሉ ተብሎ በብዙዎች ይገመታል። እንኳንና የሃገርና የወገን ጉዳይ ለመወያየት ስብሰባ ላይ መሳተፍ ቀርቶ፣ የሰይጣንም ዲስኩር ለመስማት ለሚፈልግ ግለሰብ ወይም ድርጅትም መብቱ በሕግ የተጠበቀ ቢሆንም፣ ስብሰባውን ለመካፈል ለሚፈልጉ ወገኖች እያስፈራሩ፣ እየሰደቡ፣ ፊታቸው ላይ ምራቅ እየተፉና ለመደብደብ እየቃጡ መጮህ የወንጀል ተግባር (Assault) እንጂ ከማንኛውም መንግስት ስጦታ የተሰጠ መብት አይደለም። ጭንቅላታችን ካልተደፈነና ማሰብ ካላቆመ በስተቀር ተቃዋሚ ሃይል ለመቃወም መብት እንዳለው ሁሉ እኮ ደጋፊውም እኩል መብት አለው። መላው የሰልፉ ተሳታፊዎች ባያጠቃልልም፣ በወንጀል ተግባር ላይ ለተሳተፉት ግለሰቦች ሕግ ፊት የማቅረቡ ጉዳይ በቅርቡ እንደሚጠናቀቅና ለዚሁም የምስክር፣ የቪድዮና፣ የኦዲዮ መረጃና ማስረጃ እየተሰባሰበ ክስተቱን በመቃኘት፣ ወንጀል ላይ እጃቸው ለነከሩት ግለሰቦች፣ በፖለቲካ፣

በማሕበራዊና፣ በኢኮኖሚው ዘርፍ መራራ ወቅት እንደሚሆንባቸው ሪፖርቱ አክሎ አትቷል። እነኚህ ወንጀል ላይ የተሳተፉት ግለሰቦች ከነ ተባባሪዎቻቸው ጋር፣ የሲያትል ወንጀል መከላከል ቢሮና ዓቃቤ ሕግ ክሱ ለመጀመር ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቁ ዘግይቶ ከደረሰን መረጃ ለማወቅ ችለናል። መረጃው እንዳመለከተው፣ የከተማው የፀጥታ አባሎችና የሲያትል ፖሊስ በአመፁ ምክንያት ትዕግስታቸው እንደተሟጠጠና፣ በወንጀለኞቹ ላይ፣ ለሚቀርበው ክስ ሁሉ ትብብራቸው እንደሚለግሱ፣ ከተለያዩ ምንጮች መገንዘብ ችለናል። በሚለንየሙ ወቅት (Y2K) እንደተከሰተው፣ የዳብልዩ ቲ ኦ (WTO) ዓመፅ ላይ ተሳትፈው ወንጀል ለፈፀሙ ግለሰቦች በሕግ ስርዓቱ ምን ያህል እንደተቀጡና እንደተንገላቱ፣ በህይወታቸው ላይም የደረሰባቸው ችግር የቅርብ ግዜ ትውስታችን ነው። ይሁንና የባለፈው ሓሙስ ረብሻ በሁለንተናው ከዳብልዩ ቲ ኦ ጋር ተመጣጣኝ ባይሆንም ወንጀል የመፈፀም ተግባር (Criminal Act) እስከ ሆነ ድረስ በህግ ስርዓቱ በኩል ትኩረት የሚስብ ወንጀል መፈፀሙ ብዙዎች ምስክርነታቸው ይሰጣሉ። ጉዳዩ በሲያትል ፒ አይ ጋዜጣ እንደተዘገበው ሳይሆን፣ ከዛ በባሰ መልኩ የወንጀል ተግባር እንደተፈፀመ፣ ከተለያዩ ምንጮች በተቀናበረው የኦዲዮና የቪድዮ መረጃ ለማወቅ ተችሏል። በማንኛው ሃገር ሕግ የሚረቀው ሕጉን ለሚተላለፉና ለወንጀለኞች ተብሎ እንደሆነ ተገንዝበን ባለፈው ሓሙስ የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ሂደቱና ውጤቱ እየተከታተልን እስክንዘግብላቹ ድረስ የዛሬው ሪፖርታችን በዚሁ እናጠናቅቃለን።

መልካም ሳምንት

ኢትዮ-ኦብዘርቨር ስታፍ

ሲያትል